የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሣኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
አዲስ አበባ ሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

30th Year No.41
ADDIS ABABA 11th July, 2024

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፱፻፴፮/፪ሺ፲፮

ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ...ገጽ ፲፭፯፻፩

Content

Proclamation No. 1336/2024

Expropriation of Land Holdings for Public Purpose, Payments of Compensation and Resettlement (Amendment) Proclamation .....Page 15701

አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፱፻፴፮/፪ሺ፲፮

ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ

ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ማሻሻል በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭(፪)(ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፱፻፴፮/፪ሺ፲፮ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ማሻሻያ

ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሣ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር ፭፻፲፱፻፴፮/፪ሺ፲፮ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡-

Proclamation No. 1336/2024

A PROCLAMATION TO AMEND EXPROPRIATION OF LAND HOLDINGS FOR PUBLIC PURPOSE, PAYMENTS OF COMPENSATION AND RESETTLEMENT (AMENDMENT) PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Expropriation of Land holdings for Public Purpose, Payments of Compensation and Resettlement Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(2) (a) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Expropriation of Land holdings for Public Purpose, Payments of Compensation and Resettlement (Amendment) Proclamation No. 1336/2024".

2. Amendment

Expropriation of Land holdings for Public Purpose, Payments of Compensation and Resettlement Proclamation No. 1161/2019 is hereby amended as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 85.00 ብር

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹፻፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ተሰርዘው የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) ተተክተዋል፡-

1/ Sub-Articles (2) and (3) of Article 9 of the Proclamation are hereby deleted and replaced by the following new Sub-Articles (2) and (3):

፪/ "መሬት ለህዝብ ጥቅም እንዲውል ሲወሰን የመሬት ይዞታቸውን እንዲለቁ ለሚደረጉ ባለይዞታዎች የሚከፈለው ካሣ እና የመቋቋሚያ ድጋፍ ወጪ በሚከተሉት አካላት ይሸፈናል፡-

2/ "When the land is expropriated for public purpose, payment of compensation and resettlement cost is covered by the following bodies:

ሀ) የመሬት ይዞታው እንዲለቀቅ የተወሰነው በፌደራል መንግስት ለሚከናወን መሠረተ ልማት እና የማህበራዊ አገልግሎት ማስፋፊያ ከሆነ የልማት ስራው የሚካሄድበት የክልል አስተዳደር ለባለይዞታዎች የሚከፈለውን የንብረት ካሣ ፣ የልማት ተነሺ ድጋፍ፣ የኢኮኖሚ ጉዳት ካሣ ፣ የማህበራዊ ትስስር መቋረጥ እና የሥነ ልቡና ጉዳት ካሣ ወጪ የመክፈል ግዴታ አለበት፤

a) When the land is expropriated for infrastructure and social service development to be carried out by the federal government, the Regions Administration where the development is carried on shall have the duty to make the payment for asset compensation, support to the displaced people, economic loss compensation, social ties discontinuance and moral damage compensation, to the land holders;

ለ) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት ለሚከፈለው ካሣ የሚውለው ገንዘብ የሚመደበው የፌደራል መንግስት በየዓመቱ ለክልል ከሚመድበው የበጀት ድጋፍ እንዲሁም የካሣ ክፍያን ታሳቢ ተደርጎ ለክልሎች ከሚመደበው በጀት እና ከክልሉ ገቢ ይሆናል፤

b) The money allocated for the compensation to be paid according to Sub-Article (2) letter (a) of this Article will be from the Budget support that the Federal government allocates to the Region every year, as well as from the Budget allocated to the Regions considering the compensation payment and the revenue from the Region;

ሐ) የመሬት ይዞታው እንዲለቀቅ የተወሰነው በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ) ከተገለፀው ውጪ ለሆነ የህዝብ ጥቅም ከሆነ መሬቱ እንዲለቀቅ የተወሰነለት አካል የተዘረዘሩትን ካሣዎች እና የመቋቋሚያ ወጪ ለከተማው ወይም ለወረዳው አስተዳደር ገቢ ያደርጋል፤"

c) When the land is expropriated for public Purpose other than what is provided under Sub-Article (a) of this Article, the land requiring body shall pay the required compensation and resettlement expenses to the City or Woreda Administration;"

መ) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) (ለ) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ መሠረተ ልማት ወይም ማህበራዊ

d) Subject to the provisions of Sub-Article (2) (b) of this Article, when an infrastructure or social

አገልግሎት በአንድ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ወረዳዎችን ወይም ከተማ አስተዳደሮችን የሚመለከት በሆነ ጊዜ ሥራውን የማስተባበር ኃላፊነት የክልል ሲሆን ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ክልሎችን የሚመለከት በሆነ ጊዜ ደግሞ አግባብነት ያለው የፌዴራል ተቋም ሰራውን የሚያስተባበር ይሆናል፤	service concerns two or more Woredas or City Administrations in the same region, the responsibility for coordinating the work will be to the Region, and when it concerns two or more regions. The relevant Federal Agency will coordinate the work;
ሠ) የአገልግሎት ሰጭ የመሠረተ ልማት ተቋማት መስመሮች (የኢትዮ ቴሌኮም ፣ የመብራት ኃይል እና የመንገዶች አስተዳደር) የፌደራል አገልግሎት ሰጭ ተቋማት መሠረተ ልማት መስመሮች ማዛወሪያ እና መልሶ ግንባታ ክፍያን በተመለከተ የንብረቶቹ ማዛወሪያ ወይም ማሰነሻ እንዲሁም መልሶ ግንባታ ወጭ በአገልግሎት ሰጭ ተቋማት ተገምቶ በሚቀርበው መሠረት ንብረቶቹ እንዲዘዋወሩ በሚጠይቁት የፌደራል የመሠረተ ልማት ዘርጊ ተቋማት ይሸፈናል፡፡	e) Service-providing infrastructure facility lines (Ethio Telecom, Electricity and Road Management) Federal service-providing facility infrastructure line relocation and reconstruction payment regarding the transfer or start-up and reconstruction cost of the assets as estimated by the service-providing facilities in accordance with the federal infrastructure plan that requires the assets to be moved Institutions are covered.
፫/ "የከተማ ወይም የወረዳው አስተዳደር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) መሠረት የካሣ ግንዘቡ ለልማት ተነሺው ካልተከፈለ ከመሬቱ አያስለቅቀውም፡፡	3/ "the City or Woreda Administration shall not require handing over of the land unless compensation is made to the landholder in accordance with Sub-Article (2) of this Article."
፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፳ ስር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፫) እና (፭) ተጨምረው ነባሩ ንዑስ አንቀጽ (፫) ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኖ ተሸጋሽጓል፡-	2/ the following new Sub-Articles (3) and (5) are added under Article 20 of this Proclamation and the existing Sub-Article (3) is renumbered as Sub-Article (4):
"፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) ሥር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በፌደራል መንግስት ከሚከናወኑ መሠረተ ልማት እና ማህበራዊ አገልግሎት ማስፋፊያ ፕሮጀክቶች ጋር በቀጥያዘ ፕሮጀክቶቹን የሚያስፈፅመው መሠረተ ልማት ወይም ማህበራዊ አገልግሎት አስናዋኝ ተቋም ላይ የሚቀርቡ የፌደራሉ ተቋም ተካፋይ የሚሆንባቸው ክሶች የሚቀርቡት የመሠረተ ልማቱ ወይም የማህበራዊ አገልግሎቱ የሚያከናውነው የፌዴራል	"3/ Subject to the provision under Sub-Article (2) of this Article, in relation to the infrastructure and social service expansion projects carried out by the Federal Government, lawsuits filed against the infrastructure or social service implementing institution that implements the projects, in which the Federal Institution is a party, will be submitted to first instance court where the Head quarters of the

ተቋም ዋና መስሪያ ቤት በሚገኝበት ቦታ ባለው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በክልሎች የሚከናወኑ መሰረተ ልማቶች እና የአገልግሎት ማስፋፊያ ፕሮጀክቶች ላይ እንዲሁም የፌደራል ተቋሙ ተካፋይ የማይሆንባቸው ከወሰን ማስከበር ጋር የሚያያዙ ክሶች በክልሎች እና የከተማ አስተዳደሮች ፍርድ ቤቶች የሚታዩ ይሆናል፤	Federal Institution that performs the infrastructure or social service is located. cases related to infrastructure and service expansion projects carried out by the Regions, as well as cases related to border enforcement in which the federal institution is not a party, will be heard in the courts of the Regions and City Adminfistrations;
፭/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) መሠረት የሚነሱ ማናቸውም ዓይነት የፍርድ ቤት ክርክሮችን ተከትሎ በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ የመሠረተ ልማት ወይም ማህበራዊ አገልግሎት አከናዋኝ ተቋምን የሰራ ኃላፊዎች ታስረው ውሳኔውን እንዲፈፅሙ የሚሰጥ ትዕዛዝ ፣ የልማት ስራውን እንዲታገድ የሚሰጥ ትዕዛዝ፣ የባንክ ሂሳብ የማገድ ወይም በቀጥታ ከሂሳቡ ላይ ገንዘብ ተቀናሽ ተደርጎ እንዲፈፀም የሚሰጥ ትዕዛዝ የሚሰጠው በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አማካኝነት ብቻ ይሆናል።	5/ According to Sub-Article (3) of this Article, following any kind of court arguments, an order to arrest the officials of the infrastructure or social service institution and execute the decision, an order to suspend the development work, to freeze the bank account or to deduct money directly from the account, An injunction can only be issued by the President of the Federal First Instance Court .
፫/ የአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ስር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል፡-	3/ the following new Sub-Article (5) is added under article 23 of this proclamation:
"፭/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፱ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት መሬት እንዲለቁ ለተደረጉት ባለይዞታዎች ተገቢውን ካሣ ይከፍላል ወይም እንዲከፈል ያደርጋል።	"5/ shall pay or cause to be paid appropriate compensation to land holders who have been displaced in accordance with Sub-Article (2) of Article 9 of this Proclamation."
፬/ በአዋጁ አንቀፅ ፳፮ ሥር የሚከተለው አዲስ ድንጋጌ ንዑስ አንቀፅ (፫) ሆኖ ተጨምሯል፡-	4/ Under Article 26 of the Proclamation, the following new provision is added as Sub-Article (3):
"፫/ በዚህ አንቀፅ ሥር የተቀመጡት ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በዚህ ረቂቅ አዋጅ በተደረጉ የድንጋጌ ማሻሻያዎች ዙሪያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ያወጣል።	"3/ without prejudice to the other provisions laid down under this Article, The Council of Ministers shall issue regulations regarding the amendments to the provisions of this Proclamation.
፭/ የአዋጁን አንቀፅ ፳፯ ድንጋጌ ንዑስ አንቀፅ (፩) በማድረግ የሚከተለው አዲስ ድንጋጌ ንዑስ አንቀፅ (፪) ሆኖ ተጨምሯል፡-	5/ the following new provision is added as Sub-Article (2) of Article 27 by making the existing provision as Sub-Article (1):

"፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን በፊት በነባር ፕሮጀክቶች ክፍያ በመጠባበቅ ላይ ያለ ማናቸውም የካሣ ወይም የመቋቋሚያ ወጭ ጥያቄ ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት ስራ ላይ በነበረው የአዋጅ ድንጋጌ መሠረት ፍፃሜ ያገኛል።	"2/ Subject to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, any claim for compensation or settlement costs pending payment by existing projects before the effective date of this Proclamation will be settled according to the provisions of the Proclamation that were in force before the effective date of this Proclamation.
፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።	3. Effective Date This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.
አዲስ አበባ ሐምሌ ፩ ቀን ፪ሺ፲፮ ዓ.ም	Done at Addis Ababa, on this 11th Day of July, 2024
ሣህለ ወርቅ ዘውዴ	SAHLEWORK ZEWDIE
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት	PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA